በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

የቆሎ ተማሪ

ከሞቀው ቤት ከእናት ማጀት

ከወንድም ፍቅር

ከእህት ስስት

የነጠለኝ ከአያት ቁጣ

ያስታጠቀኝ አጭር ቁምጣ

አንጠልጥዬ ያኮፋዳ

የዞርኩትኝ ጋራ ሜዳ

በእዝናት ልብስ በባዶ እግር

የለፋሁት ከገዳም ደብር

ከየኔታ የኔታ የትናየት ሀገር አልፌ የተጓዝኩት

እንዳይመስልህ ደግ ስሜን በክፉ ቃል እንድትናኙት

እዚያ ት/ቤት አገር ጥዬ ስሰነብት

በስመአብ ዳዊት ድጋም ጠዋት ቁርሴ

ቀን ልመና ከየሰዉ ቤት ትንሽ ጉርሴ

ከሰው በራፍ በእንተ ማርያም

ከውሻ ጋር ትግል መግጠም

ተወው ውሻውን ውሻ እንኳን ሀቅ አለው

ከአሁን ባይብስም ሰው ሁሉ ጠላቴ ነው

ዝናብ ካልዘነበ የገበሬ ደሙ በኔ ላይ መራር ነው

ከዛም ከቀኑ መልስ ማታ በሰባር ሀሊና

በሰባር ሀሊና በመንፈስ ደስታ

አንዱ ቅኔ አንዱ ዜማ

ከአርያም ደብረ አባይ ድምፃችን ሲሰማ

ሥጋ ሲሞላ በቃል ትምህርት

ነፍስ ስትነጠቅ ከሰማያት

ሥጋ ብቻውን በድኑን ሲቀር

በየኔታ ቅኔ ስንል እጹብ መንክር

ፍቅሩ ነበር የለየኝ

መከራውን ያስታገሰኝ

ከመቅደስ ጎጇችን ከጫካው ያቆየኝ

እንደሰማያት ምስጋና

እንደሱራፌል ሱባሔ

ሀሌሉያ ሲባል ሀሌሉያ ሆይ

ድካም የለ ታላቅ ደዌ

ዓለምን ሰቀልናት ከመግህፍት ቤት

በትርጓሜ በሊቃውንት

ፍቅሩ ነበር የለየኝ

መከራውን ያስታገሰኝ

ከመቅደስ ጎጇችን ከጫካው ያቆየኝ

ከየኔታ የኔታ የትናየት ሀገር አልፌ የተጓዝኩት

እንዳይመስልህ ደግ ስሜን በክፉ ቃል እንድትናኙት

ጎንደር ዜማ ሞዛ መፅሐፍ ቅኔ ዲማ

ሸዋ ላይ አንኮበር አስመራ ላይ ቢዘን

ደብረ ሀሌሉያ የተጓዝኩት አክሱም ጽዮን

ቦሩ ሥላሴ ሽንጤን ገትሬ

የታገልኩት በፍካሬ

ፍቅሩ ነበር የለየኝ

መከራውን ያስታገሰኝ

እናም ልጇ አልርገምህ

አባ እንድትለኝ ገና እንኳን ሳልፀንስህ

ከየኔታ የኔታ የትናየት ሀገር አልፌ የተጓዝኩት

እንዳይመስልህ ደግ ስሜን በክፉ ቃል እንድትናኙት!